ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ

**Coalition for Unity and Democracy Party (Kinijit)**

http://www.kinijitethiopia.org

e-mail kil@kinijitinternational.org Voice Mail/Fax 1-206-203-3974

ጋዜጣዊ መግለጫ

ኪል-001/07
ታህሳስ 24 ቀን 1999 ዓ.ም

# ትናንትም፣ ዛሬም ዋንኛው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ደህንነት፣ ጥቅምና ህልውና አደጋ ወያኔ/ኢህአዴግ ነው::

የቅንጅት ልዩ መለዮ የፓርቲው መሰረታዊ አላማ ሃገርን ማዳን ነው ብሎ መነሳቱ ነው:: የኢትዮጵያ ህዝብም ለአስራ ሰባት አመት ወያኔ ያካሄደበትን በዘርና በሃይማኖት የመከፋፈልን የስነልቦና ጦርነት ተቋቁሞና ወያኔ የዘረጋውን የዘር የፖለቲካ ስርአት ተቃውሞ በግንቦት 1997 ለቅንጅት ከፍተኛ ድጋፉን የሰጠው ይህ ሃገር የማዳን የቅንጅት ተልእኮ ከየትኛውም ሃገራዊ ተልእኮ አንገብጋቢና የተባረከ ነው ብሎ ስላመነ ነው:: የስልጣን እሽቅድድም ከሚያመጣው ቀውስ ይልቅ ሃገራዊ መረጋጋትን፣ ከእልህ ይልቅ መቀራረብን፣ ከአመጽ ይልቅ ሰላምን፣ ከበቀል ይልቅ እርቅን፣ ከጠባብ ቡድነኛነት ይልቅ ስፋት ያለውን አንድነትን አጥብቆ በመያዝ የቅንጅት መሪዎች አባላቱና ደጋፊዎቹ አይችሉትን እየቻሉ ለእነዚህ የሀገር ማዳኛ ናቸው ብለው ላመኑባቸው እሴቶች መስወእትነት እየከፈሉ ነው::

ቅንጅት እንደወያኔ «እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል» በሚል አውዳሚ ብሂል የሚመራ ድርጅት አይደለም:: ይህ በመሆኑም ነው ይህን ሃገር ለማዳን ለህዝብ የገባውን ቃል ኪዳን ለመጠበቅ በየትኛም ወቅት የሃገራችንን ህልውና አደጋ ላይ ሊጥሉ ይችላሉ ተበለው የሚነሱ ጉዳዮችን በከፍተኛ አትኩሮት የሚያጤናቸው:: ወያኔን/ኢህአዴግ በሱማሌ ግዛት ያሳየውን ጣልቃ ገብነት በሚመለከትም ህዳር 17 1999 ቅንጅት የሰጠው መግለጫ በእዚሁ ሀገርን ለማዳን ቅድሚያ ከሚሰጠው የአመለካከት ማእቀፍ የተቃኘ ነው:: ከብሄራዊ ደህንነታችን ጥቅምና ህልውና አኳያ የተፈጠረው ቀውስ የሚኖረውን ትርጉም በመመርመር ነው::

ወያኔ በሱማሊያ ውስጥ አለ ብሎ የሚነግረንን የኢትዮጵያ ብሄራዊ ደህንነት አደጋ «ከመቼ ጀምሮ ነው ሰለኢትዮጵያ ደህንነት ወያኔ ተቆርቋሪ የሆነው ብሎ ቅንጅት አላጣጣለውም:: ወያኔ በሃገራችን ደህንነትና ጥቅም ላይ በተከታታይ የፈጸመውን ወንጀል በመጥቀስ አናዳምጥም አላለም:: ወያኔና ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች የተካኑበትን በርቀት የማያሳይ ብሂል በመጠቀም «የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው:: በኢትዮጵያም ኪሳራ ቢሆን ወያኔ ላይ ጉዳት እስከደረሰ ምንቸገረን» ከሚል ቅኝት ሁኔታውን አላየውም::

በሱማሊያ አለ የተባለውን አደጋ በወቅቱ ከነበረው መረጃ በመነሳት በጥሞና በማጥናት ቅንጅት የወሰደው አቋም፣ አደጋው ከሚገባው በላይ በወያኔ የተጋነነ፣ ወያኔ በሃገር ብሄራዊ ደህንነትና ጥቅም ላይ በሃገራችን ውስጥ አየፈጸመ ካለው አደገኛ ድርጊት ጋር ሲወዳደር ኢምንት መሆኑን የሚያሳይ ነበር::

አቋማችን ትከክለኛ ለመሆኑ ወያኔ በወታደራዊና በመሳሪያ አቅማቸው በከፍተኛ ደረጃ ተደራጅተው የሃገራችንን ብሄራዊ ደህንነት አደጋ ላይ ሊጥሉ አንድ ጀንበር ቀርቷቸዋል ያላቸው የእስልምና ፍርድ ቤቶችና ሰራዊታቸው እፍ ቢሏቸው ብን ያሉ በመሆናቸው ተረጋግጧል:: ወያኔ በሱማሊያ ያለው አደጋ የሚያጋንን፣ የተሳሳተ መረጃ ለኢትዮጵያ ህዝብና ለአለም አቀፍ ህብረተሰብ ለማቅረብ የተገደደው ይህንንም አደጋ አሳቦ በሱማሊያ ውስጥ ጣልቃ ለመግባት የፈለገው በሃገር ውሰጥ ለፈጸመው ወንጀል ተጠያቂ የሚያደርገው በሃገር ውስጥና ከሃገር ውጭ የተጀመረው ትግል የማይበርድ መሆኑን ስለተገነዘበ ነው ብለናል:: አላማው ሃገሬውንና አለምአቀፉን ህብረተሰብ ለማዘናጋትና የትኩረቱን አቅጣጫ ለማሳት እንደሆነ ጠቁመን ነበር::

ወያኔ በብሄራዊ ደህንነት ስም በሱማሊያ ላይ ያካሄደውን ወራራ በሽፋንነት በመጠቀም በሃገር ውስጥ በህዘባችን ላይ የሚያኪያሂደውን የግፍ እርምጃ አጠናክሮ ቀጥሎበታል:: ባለፉት አስራ አምስት ቀናት ውስጥ ብቻ የቅንጅትና የሌሎች ተቃዋሚ ድርጅቶች አባላትና ደጋፊዎች ናቸው የሚላቸውን በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ግለሰቦችን እያደነ ለእስር መዳረጉና ጥቂቶችንም መግደሉ ቀድመን ለገለጽነው ስጋት በቂ ማስረጃ ነው::

በሃገር ውስጥም ሆነ ከሃገር ውጭ የሚገኘው ኢትዮጵያዊ ወያኔ ስራዬ ብሎ ባጠመደለት የሶማሊያ አጀንዳ ዙሪያ ሲነጋገር፣ ወያኔ በሃገር ውስጥ በምርጫ 1997 ድምጽ የነሱትን ዜጎች ስቃይ ለማራዘም የአፈና ስራውን እያጧጧፈና በእዚህ ቀውስ ስም ከውጭ መንግስታት በሚያገኘው የገንዘብ፣ የወታደራዊና የስለላ ቁሳቁስ ድጋፍ የአፈና መዋቅሩን እያደራጀ ይገኛል:: የአለምአቀፉን ህብረተሰብ ትኩረትም በኢትዮጵያ ወስጥ ወያኔ ካኪያሄደውና እያካሄደ ካለው የሰብአዊና የዴሞክራሲ መብቶች እረገጣ፣ የፍትህ እጦት፣ የጅምላ ግድያና እስራት ላይ መሆኑ ቀርቶ የአለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃን ከፍተኛ ሽፋን እንዲሰጡት በተደረገው የሱማሊያ ቀውስ ላይ እንዲሆን ተደርጓል:: ለእዚህ ነው ቅንጅት ይህንን አደገኛ አዝማሚያ በአስቸኳይ በመገንዘብ አባላቱ፣ ደጋፊዎቹና አጠቃላይ የሃገሪቱ ዜጎች ለብሄራዊ ጥቅማችን መከበር አስፈላጊ የሆነውን የነጻነት፣ የዴሞክራሲና የአንድነት ትግል

ለማዘናጋትና ለማምታታት ወያኔ ከሚፈጥራቸው ትእይንቶች ባሻገር ማየት ይኖርብናል የሚለው፡፡ ከሃገራችን ብሄራዊ ህልውና ጥቅምና ደህንነት በመነሳት ባለንበት ወቅት ለሚታየው አጠቃላይ ቀውስ ዛሬም ምላሹ፤

- በአካባቢያችን የሚታየውን ቀውስ ለመፍታት አለም አቀፍ፣ አህገራዊና ክባቢያዊ ድርጅቶች ሃለፊነታቸውን እንዲወጡ መጠየቅ ነው፡፡ ከኢትዮጵያ የዘለቄታ ብሄራዊ ጥቅምና ደህንነት አንጻር የአለም አቀፍ፣ አህጉራዊና አከባቢያዊ ድርጅቶች ስልጣን የሚሸረሽርበትንና ሃላፊነታቸው የሚዳከምበት፣ መንግስታት በሌሎች ሀገሮች ጉዳይ በተናጠል አንዳሻቸው የሚገቡበት ሁኔታ በተለይ ኢትየጵያን የመሰሉ ያላደጉ ሃገሮችን የበለጠ የሚያስጠቃ በመሆኑ ከሱማሊያ የውስጥ ጉዳይ ወያኔ እጁን እንዲያወጣ፣ በሱማሊያ ያለውን ችግር ለመፍታት ሃለፊነቱን የተጠቀሱት አለምአቀፍ አህጉርና አከባባዊ ድርጅቶች እንዲረከቡ ጥሪ ማድረግ ነው፡፡
- ባለንበት ወቅት የኢትዮጵያ ህዝብ የብሄራዊ ህልውናውና ደህንነቱ ዋንኛ አደጋዎች በወያኔ የተቀመሩ መሆናቸውን እንዳይዘነጋ ማድረግና በወያኔ አማካይነት የሚካሄደው ህዝብን በዘርና በሃይማኖት የመከፋፈል ድርጊት መሆኑን መረዳት ነው፡፡ የዜጎችን ነጻነት ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብት እንዳሻው የሚረግጠው፣ በእርቅ፣ በሰላም፣ በአንድነት፣ ለሚገነባ ጠንካራ ኢኮኖሚ፣ ፍትህን፣ ነጻነትን፣ እኩልነትንና ዴሞክራሲን መሰረት በማድረግ ለሚቋቋም የፖለቲካ ስርአት የሚቀርብለትን ምልጃ በእብሪት አልቀበል ያለው ዘረኛና አድሎኛ የሆነውን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ስርአቱን ከቀድሞው በባሰ መልኩ በማጠናከር ላይ ያለው ወያኔ መሆኑን አጥርቶ መገንዘብ ነው፡፡ ከዘረኛነትና ከአንድ ቡድን አገልጋይነት የጸዳ የፍትህና የመገናኛ ብዙሃን ስርአት እንዲኖር፣ በህዝብ የሚወደድና የሚደገፍ የአንድ ፓርቲ ወይም ግለሰብ ታዛዥ የማይሆን፣ ተገዥነቱ ለህገ-መንግስታዊ ስርአት የሆነ ጠንካራ የመከላከያ ሃይል በጋራ እንገንባ የሚለውን ጥሪ በእብሪት የሚያጣጥለው ወያኔ እንደሆነ ከምር መቀበል ነው፡፡ በእዚህ ግንዛቤ ላይ ቆሞ በሃገርና ከሃገር ውጭ የሚደረገውን ትግል በብልሃት በትእግስትና በቁርጠኛነት መግፋት ነው፡፡
- በሃገር ውስጥ በድርጅታዊ አቅም ላይ የተመሰረተ፣ በሃገራችን ዴሞክራሲያዊ ስርአት እንዲገነባ ፍላጎት ያላቸውን ሃይሎች በሙሉ በማስተባበር፣ የህዝባዊ እምቢተኛነት ትግል ማቀጣጠል ነው፡፡ ወያኔ በግፍ ያሰራቸውን የፖለቲካ ድርጅት መሪዎች፣ የሲቪክ ማህበራት ተወካዮችን፣ የነጻው ፕሬስ ጋዜጠኞችንና በተለያዩ የፖለቲክ ድርጅቶች በአባልተነትና በደጋፊነት ብቻ በሽዎች በየማጎሪያው ጣቢያ ያጎራቸውን የህሊና እስረኞች ባስቸኳይ በመፍታት ለቀረበለት የእርቅና የውይይት ጥሪ አዎንታዊ ምላሽ እንዲሰጥ መታገል ነው፡፡
- ከሃገር ውጭም የሚገኘው ሃገር ወዳድ የሃገራችን ህዝብ በሃገሩ ላይ የሚያደርገውን ትግል ወሳኝነት በመረዳት ሃብቱን እውቀቱን እና ጉልበቱን በጋራ በማቀናጀት የወገኑን ትግል መደገፍ ነው፡፡ ከጠባብ ብሄራዊ ጥቅማቸው በመነሳት ወያኔ በሃገራችን ውስጥ የሚፈጽመውን የሰብአዊና የዲሞክራሲ ረገጣ ቸል የሚሉትን የውጭ መንግስታት ይህ ቸልታቸው ውሎ አድሮ የኢትዮጵያን ሰላምና መረጋጋት አደፍርሶ አካባቢውን የጽንፈኞች መናኀሪያ ሊያደርገው የሚችል መሆኑን ማስረዳት ነው፡፡ በአፍሪካ ቀንድ አለ ወይም ሊፈጠር ይችላል በማለት የሚያሰጋቸው የጽንፈኛነት እና የአሸባሪነት አደጋ በዘላቂነት መከላከል የሚቻለው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚደረገውን የነጻነትና የዴሞክራሲ ትግል በመደገፍ ብቻ መሆኑን ሳይታክቱ ማስረዳት ነው፡፡ ወያኔ የፈጸማቸውንና የሚፈጽማቸውን ኢሰብአዊ እርምጃዎች አለምአቀፉ ህብረተሰብ፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ በሚገባ እንዲያውቁት በማድረግ ወያኔን የሚደግፉ መንግስታት ከራሳቸው ህዝብና ተቋማት ተጽእኖ እንዲደርስባቸው ለማድረግ የጀመረውን ስራ አጠናክሮ መቀጠል ነው፡፡
- በመጨረሻም ሁሉም ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ፣ ዛሬ ኢትዮጵያና ህዝቧ ያሉበትን አደጋ የሚገነዘቡ የፖለቲካ፣ የሲቪክ፣ የሰብአዊ መብት ተሟጋችና ተከራካሪ ድርጅቶች በሙሉ፣ ወያኔ ለዴሞክራሲና ለነጻነት የምናደርገውን ትግል ለማዘናጋት በየግዜው በሚፈጥራቸው ትርኢቶች መወናበድ የለብንም፡፡ በማያልቀው ጥበቡ ወያኔ የሚጭረውን እሳት ለማጥፋት መንደፋደፍ፣ ባጠመደው የትኩረት አጀንዳ በመጠለፍና በተለመደው ወጥመድ ውስጥ በመውደቅ የኢትዮጵያና የህዝቧ ህልውና አደጋ ላይ የጣለውን ዘረኛና አምባገነናዊ የሆነው የወያኔ የፖለቲካ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ስርአት መሆኑን ለአንድ አፍታም መርሳት የለብንም፡፡
- ትከረታች የሶማሊያን ወረራና ሌላም ወደፊት ወያኔ የሚፈጥረውን ግርግር በሽፋንነት በመጠቀም በእስር በሚገኙ የቅንጅትና የሌሎች ፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎች አባላትና ደጋፊዎች በጋዜጠኞችና የሲቪክ ማህበራት ተወካዮች ላይ በመለስ ዜናዊ ትእዛዝ የወንጀለኛነት የግፍ ፍርድ ለማስተላፍ እየተሸረበ ያለውን ሴራ ማጋለጥ መሆን ይኖርበታል፡፡ አሁንም ቢሆን ለሀገራችን አና ለህዝቧ የሚበጀው ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የፖለቲካና የህሊና እስረኞችን በሙሉ በመፍታት በሃገራችን የፖለቲካ ጉዳይ ያገባኛል ከሚሉ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪልና ሌሎች ተቋማት ጋር ከልብ መስራት መሆኑን ሁላችንም አምነን በሃገር ውስጥና ከሃገር ውጪ በምናደርገው ትግላችን ወያኔን ማስገደድ ይኖርብናል፡፡

**የኢትጵያ ብሄራዊ ደህንነት ጠላቶች ዘረኛነት እና አምባገነናዊነት ናቸው!**
**ለነጻነት ለዴሞክራሲ ለእኩልነትና ለአንድነት መከበር በጋራ እንነሳ!**

## ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ